


"ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም" (ምሳሌ22፥6)።

# ለልጅዎ የተቃና አስተዳደግ አጋዥ ይፈልጋሉ?

የልጆችዎ የነገ ዕጣ በእርስዎ የአስተዳደር ጥበብና በአስተዳደጋቸው ይወሰናል። እርስዎ ለልጅዎ የሚያስቡ ከሆነ አጋዥ አለዎት። የደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሕጻናትና ታዳጊ ወጣቶች የወላጆቻቸውን ሃይማኖትና ኢትዮጵያዊ ባሕል ጠንቅቀው አውቀው ለወላጆቻቸው የሚታዘዙ፣ የቤተ ክርስቲያናቸውን ሕግና ሥርዓት የሚያከብሩና በዜግነታቸው የሚኮሩ አደራ ተቀባይ ዜጎች እንዲሆኑ ለማድረግ ቤተሰብን የሚያግዝ የትምህርት ፕሮግራም ለመክፈት ዝግጅቱን አጠናቋል። ትምህርቱ የሚሰጠው በሙያው የቆየ ልምድ ባላቸው አስተማሪዎች ነው።

- ✓ ትምህርቱ የሚያካትታቸው የኮርስ ዓይነቶች፣
    1) ቋንቋ (አማርኛ)፣
    2) ያሬዳዊ መዝሙርና የቅዳሴ ተሰጥኦ፣
    3) ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር (መጽሐፍ ቅዱስ)፣
- ✓ ትምህርቱ የሚሰጥበት ቀን ዘወትር ቅዳሜ ከ9፡00AM -11:00AM፣
- ✓ ትምህርቱ የሚሰጥበት ቦታ **1710 Moorpark Ave San Jose, CA 95128**፣

**ዕድሉን ይጠቀሙበት።**

*በስልክ ቁጥር (408)219-2437 ደውለው ይመዝገቡ፣*

ማሳሰቢያ፡- ፕሮግራሙ ከላይ ከተዘረዘሩት አገልግሎቶች በተጨማሪ የተለየ ችግር ያለባቸው ወጣቶችና ቤተሰቦቻቸው ፕሮፌሽናል በሆኑ አማካሪዎች ቤተሰባዊ የምክር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ አመቻችቷል። ይህ አጠቃላይ የትምህርት ፕሮግራም መጠነኛ የአገልግሎት ክፍያ የሚኖረው ሲሆን የክፍያው መጠን በስምምነት የሚወሰን ይሆናል፣ ይመዝገቡ።

# DO YOU NEED HELP FOR A PERFECT UPBRINGING OF YOUR CHILDREN?

Environmental factors and family management could affect children's future life. Living in a multicultural society, you might have concerns about your child's upbringing. Debre Selam St. Michael Ethiopian Orthodox Tewahedo Church has accomplished its plan to open a school for children of Ethiopians to enable them retain their cultural heritage, be proud of their own identity, respect their parents, stay firm in the Christian Orthodox tradition and be accountable for their own belief. Here is the information you need:

- ✓ Courses given:
    1) Language (Amharic)
    2) St. Yared's Traditional Hymns (Mezmur) and Divine Liturgy (Qidassie)
    3) Christian Ethics (Biblical Study)
- ✓ Time: Every Saturday 9:00AM -11:00AM
- ✓ School address: 1710 Moorpark Ave San Jose, CA 95128

Do not miss this opportunity.
Call and register by phone
*(408)219-2437*

**N: B:** With the purpose of fulfilling the moral obligation entrusted to our Church to be a strong center of ethics, we provide individual and group counseling and psychosocial education to families with special problems to minimize cultural gaps between parents and their children and create a stable family relationship. Service fees are negotiable. Please call and register now.

# [illegible] ነው።

"ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም" (ምሳሌ22፥6)።

ሀገሩንና የሚወድና ሃይማኖቱን የሚያከብር ዜጋ ለልጆቹ የሚያወርሰው ታሪክን፣ ቋንቋን፣ ሃይማኖትንና ባህልን ጭምር ነው እንጅ ገንዘብና ንብረትን ብቻ አይደለም። በግብፅ ሀገር በስደት ይኖሩ ከነበሩ እስራኤላውያን እናቶች መካከል አንዷ ዮካብድ የተባለች ሴት ድኃ በመሆኗ ለልጇ የምታወርሰው ንብረት አልነበራትም። ነገር ግን ዮካብድ የታሪክና የባሕል ድህነት እንጅ የገንዘብ ድህነት የማያሳስባት አስተዋይ ሴት በመሆኗ ለልጇ የአባቶቹን ሃይማኖትና ቋንቋ እያስተማረች አሳደገችው። በዚህም ምክንያት ልጇ ሙሴ በስደት ሀገር መኖሩ ለታሪሁና ለባሕሉ ያለውን ታማኝነት ሳያደበዝዘው አድጎ የሀገር መሪ፣ የሃያማኖት አባት ለመሆን በቃ። ስደተኛውን ሕዝብ መርቶ ወደ ሃገሩ ለመመለስም በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ አደራ ተጣለበት።

የወገኖቹን ቋንቋ፣ ታሪኩንና ባህሉን የማያውቅ ልጅ ምንም ያህል እውቀትና ገንዘብ ቢኖረው ሀገሩን ሊመራና ሕዝቡን ሊያስተዳድር አይችልም። በስደት ሀገር የተወለዱ ወይም በልጅነታቸው መጥተው የወገናቸውን ቋንቋ መናገር የማይችሉ ልጆች ከኅበረተሰቡ ጋር ይቅርና ከወላጆቻቸው ጋራ እንኳን ተግባብቶ ለመኖር ምን ያህል ችግር እንዳለባቸው በምንኖርበት ሀገር በሰሜን አሜሪካ በግልጽ የምናስተውለው እውነታ ነው።

ልጆቻችን እንደ ሌላው ኅብረተሰብ የወላጆቻቸውን ቋንቋ አቀላጥፈው አለመናገራቸው ለወደፊቱ የቤተ ክርስቲያን ዕጣ አስጊ መሆኑ ሳያንስ፣ በየቤተ ክርስቲያኑ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና የአውደ ምሕረት ውዝግቦችን እየተመለከቱ ማደጋቸው እንደ ሙሴ ሀገሩን የሚመራና ሃይመኖቱን የሚጠብቅ ታማኝ ዜጋ የማግኘታችንን ዕድል የመነመነ ያደረገዋል። መፍትሔውን መፈለግ ያለብን አሁን ነው። ይኸውም:-

1) የመንኖረው ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለሀገራችን፣ ለልጆቻችንና ለነገው ትውልድ ጭምር በመሆኑ የሰከነ አእምሮና የበሰለ አስተሳሰብ አዳብረን በተለይ የአውደ ምሕረት አለመግባባቶችን በውይይት ለመመፍታት መሞከር፤
2) በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የተጠናከረ የልጆች ትምህርት ቤት እንዲከፈት ማድረግና የትምህርቱን አሰጣጥ በንቃት መከታተል።

ከዚህ መሠረተ ሐሳብ በመነሳት የደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አዲስ የልጆች ትምህርት ቤት መከፈቱን ሲያበስር ይህ አደራ የተጣለባቸው አስተማሪዎች ልምድ ያላቸውና ኃላፊነታቸውንም በብቃት የሚወጡ መሆኑን በመተማመን ነው። ትምህርት ቤቱ ከየትኛውም አቅጣጫ የሚመጡ ልጆችን ለማስተናገድ በሩ ክፍት ነው። በዕድሉ ይጠቀሙ። ለዚህም በስተጀርባ ያለውን ማስታዎቂያ የመልከቱ።

የልዑል እግዚአብሔር ቸርነት፣ የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የታላቁ መልአክ የቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት አይለየን አሜን።

ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል
ሳን ሆዜ
ካሊፎርንያ